# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 176 መስከረም 18 2004 ገጽ 1


“ለስድስት ተከታታይ ዓመታት ከአስር በመቶ በላይ የኢኮኖሚ እድገት አሳይተናል” የሚለው ዓይን ያወጣ ውሸት፤ “ድህነትን ተረት እናደርጋለን” የሚለው ጉረኛ መፈክር፤ የወያኔዎችና ጀሌዎቻቸው በፎቅና ቪላዎች መንበሽበሽ፤ ለም መሬቶች በአበባ እርሻዎች መተካታቸው እና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ ”የህዳሴ ብስራቶች” ለሕዝባችን ምሳና እራት አልሆኑም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-3)

## ለመስከረም 21 ሰላማዊ ሠልፍ በመጥራታቸው ከታሰሩት አንዱ የሆኑት አቶ ክንፈ ሚካኤል ደበበ ከወያኔ አቃቤ ህግ ጋር ፍርድ ቤት ተብየው መድረክ ላይ መወዛገባቸው ተሰማ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አለኝ በማለት በሚኩራራው ህገ መንግሥት በመተማመን ለነገ መስከረም 21 ቀን በአዲስ አበባ ከተማ ወስጥ የሚካሄድ ሰላማዊ ሰልፍ ለማዘጋጀት ሲንቀሳቀሱ በወያኔ ደህንነትና ፖሊስ ተይዘው እስር ቤት ከተወረወሩት የሰላም ታጋዮች መካከል አቶ ክንፈ ሚካኤል ደበበ፣ ወጣት ተስፋሁን አናጌ፣ ወጣት ታምራት ሻማና ሌሎች ከእነሱ ጋር የታሰሩ 3 ግለሰቦች በትናንትናው እለት ፍርድ ቤት ቀርበው እንደነበር የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና ገለጸ።

ታሳሪዎቹ ወያኔ የፖለቲካ ባላንጣዎቹን ሞራል ለመስበርና ለመቅጣት በሚገለገልበት ፍርድ ቤት ተብዬው ሲቀርቡ ለሆዳቸ ያደሩና የባንዳነት ተግባር በማከናውን የ ዕለት ጉርሳቸውን የሚሸፍኑ አቃቤ ህጎች ፤ ግለሰቦቹ የተያዙት በውጭ አገር ከሚገኙ አሸባሪ ድርጅቶች ጋር በመሆን መስከረም 21 ቀን 2004 ዓም ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ወረቀት ለመበተን ሲዘጋጁ እጅግ ከፍንጅ ተይዘዋል የሚል ክስ እንደመሰረቱባቸው ሲገልጽ ችሎት ተብዬው ቦታ ላይ የተሰየመቺው ሴት ዳኛ በአቃቢ ህጉ የቀረበውን ክስ አምናችሁ ትቀበላላችሁ ወይስ ትቃወማላችሁ በማለት ጥያቄ አቅርባ እንደነበር የደረሰን ዜና አመልክቶአል።

ከዚያ ቦኋላ አቶ ክንፈሚካኤል ብድግ ብለው፣ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ እርሳቸውና አብረዋቸው የታሰሩት በማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ መደብደባቸውን፣ እግራቸው ወደ ላይ እራሳቸው ወደ መሬት ተዘቅዝቆ በግንድ ላይ ታስረው መገረፋቸውንና ዘርን የሚያንቋሽሽ ስድብ መሰደባቸውን በመግለጽ፣ አብረዋቸው የታሰሩት በሙሉ ንጹህን ሰዎች በመሆናቸው ሀላፊነቱን እርሳቸው እንደሚወስዱ በድፍረት በመናገር የዳኛዋንና አቃቤ ህግ ተብዬዎችን ቅስም መስበር መቻላቸውን ሂዴቱን የተከታተሉ ምንጮች ለዘጋቢያችን አስረድተዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በስዊድን የሚገኙ አትዮጵያውያን የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ

ነዋሪነታቸው በስዊድን የሆኑ ኢትዮጵያውያን ትናንት መስከረም 19 ቀን 2004 ዓም በስዊድን ዋና ከተማ ስቶክሆልም ከአገሪቱ ፓርላማ ፊት ለፊት ባደረጉት የተቃውሞ ሰልፍ ወያኔ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ሲል ያለአግባብ በእስር ቤት ያጎራቸው የፖለቲካ እስረኞችና ጋዜጠኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ጠይቀዋል።

ሰልፈኞቹ በያዙዋቸው መፈክሮች መለስ ዜናዊ በዘጎች ላይ ለፈጸመው ፍጅት ለፍርድ ይቅርብ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ባለቤት ይሁን፣ መጻፍና መናገር ሽብርተኝነት አይደለም፣ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ይቁም፣ ህዝብ ለነጻነት የሚያደርገው አመጽ በመለስ አይታፈንም፣ አሸባሪው ርእዮት ሳትሆን መለስ ና አገዛዙ ናቸው ፣ አሸባሪው አንዱአለም ሳይሆን መለስ ነው ፣ አሸባሪው እስክንድ ነጋ ሳይሆን መለስ ነው ፣ ኢትዮጵያ የመለስ ዜናዊ እስር ቤት አትሆንም፣ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ትሆናለች የሚሉት ይገኙበታል።

በሰላማዊ ሰልፉ ላይ የአገሪቱ ጋዜጠኞች በብዛት መገኘታቸውን፣ የስዊድን የተለያዩ ፓርቲዎች አባላትና መሪዎችም መገኘታቸውን ዘጋቢያችን ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ሂውማን ራይትስ ወች የእንግሊዙን የልማት ሚኒስትር ወቀሰ

የአለማችን ጠንካራው የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች የሆነው ሂውማን ራይተስ ወች ለእንግሊዙ የውጭ የልማት ትብብር ሚኒስትር አንዲሪው ሚቼል በጻፈው ደብዳቤ፣ ባለስልጣኑ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው የውጭ እርዳታ ኢትዮጵያውያንን ለመጨቆኛነት መዋሉን ማረጋገጥ አልቻልም በማለት ለቢቢሲ የሰጡት ቃል ተአማኒነት የሌለውና ህዝብን ሆን ብሎ ለማደናገር የቀረበ ነው በማለት ወቅሷል።

ሂውማን ራይትስ ወች ለኢትዮጵያ የሚሰጠው እርዳታ ለተገቢው ህዝብ ከሚደርስ ይልቅ የመለስ መንግስት የፖለቲካ ደጋፍ መግዢያ ማዋሉን ለሚኒስትሩና በኢትዮጵያ ለእንግሊዝ አምባሳደር በተደጋጋሚ ቢያሳውቁም፣ ምንም ምላሽ ሳይሰጥ መቆየቱን አስታውሷል።

ሂውማን ራይትስ ወች፣ አንድሪው ሚቼል የእንግሊዝ መንግስት እርዳታ ለኢትዮጵያ መንግስት በቀጥታ አይደርስም ብለው የተናገሩት ፍጹም ተአማኒነት የሌለው ነው ካለ በሁዋላ፣ እንግሊዝ ለኢትዮጵያ የምትሰጠው እርዳታ በቀጥታ የኢትዮጵያ መንግስት እንደሚጠቀምበት የእንግሊዝ አምባሳደርም ሆነ የአሜሪካ መንግስት የሚያቁት ጉዳይ ነው ብሎአል።

እርዳታው ለክልል መንግስታት ቢሰጥም የክልል መንግስታትን በቀጥታ የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት ነው የሚለው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የህዝባችንን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል የአባይን ወንዝ እገድባለሁ ብሎ የተነሳው ወያኔ ለግድብ ማሰሪያው የህዝብ መዋጮ አነስተኛ በመሆኑ የግል ባለሀብቶች እንዲሳተፉበት ጥሪ እንዳቀረበ ተዘገበ

የአባይ ግድብ የህዝብ አደራጅ ኮሚቴ ተብሎ የተቋቋመው ድርጅት ሀላፊ የሆነው በረከት ስምኦን ለብሉምበርግ እንደተናገረው ፣ የመንግስት ሰራተኛው ከደሞዙ እየቀነሰ የአባይን ግድብ ቦንድ እንዲገዛ መታዘዙ የሚያዛልቅ አልሆነም በማለት ቀደም ሲል ከፍተኛ የህዝብ መነቃቃት ታይቶበታል ተብሎ በወያኔና ተባባሪዎቹ ሚዲያ ሲራገብ የነበረውን ባዶ ፕሮፖጋንዳ አጋለጠ።

ላለፉት በርካታ ወራት ጠዋትና ማታ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ለግድቡ ማሰሪያ ገንዘብ እያዋጣ ነው እንዳልተባለ እስከዛሬ የተዋጣው 7 ቢሊዮን ብር ብቻ እንደሆነና ቀሪውን 80 ቢሊዮን ብር ለማግኘት የግሉ ክፍል እንዲሳተፍ ጥሪ መቅረቡን የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ተቀጽላ የሆነው በረከት ተናግሮአል። በስልጣን ላይ ያላቸውን ቆይታ ለአንድ ቀን እስከአራዘመ ድረስ ህዝብ ፊት ወጥተው የሚናገሩት ውሸት ከማያሸማቅቃቸው አንዱ የሆነው በረከት ስም ያን እንደተናገረው የግሉ ባለሃብቶች ካልተሳተፉ በቀር የግድቡን ወጪ ለመሸፈን አዳጋች እንደሆነ አልደበቀም።

አስተያየት ሰጪዎች ግን ይህን ግዙፍ ግድብ አለ ውጭ እርዳታ መስራት እንደማይቻል ገልጸው፣ ምናልባትም መስራት የሚችል የአገር ውስጥ የግድል ድርጅት ካለ የህወሀት ንብረት የሆነው ኢፈርትና አለሙዲ ናቸው ይላሉ።

ኢፈርትና የአላሙዲ ድርጀቶች በጋራ ግድቡን ሊያስጨርሱ እንደሚችሉ የሚናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፣ ይህም ቢሆን አገሪቱ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ ሙሉ በሙሉ በሁለቱ ድርጅቶች እንዲገባና የአባይ ባለቤትነት የኢፈርትና የአላሙዲ እንደሚሆን እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።

ከኢፈርት ና ከአላሙዲ ድርጅቶች ውጭ ያሉ የግል ድርጅቶች በሀይል ቦንድ እንዲገዙ የሚገደዱ ከሆነ ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚገድለው አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

የአባይ ግድብ ፕሮጀክት ይፋ የሆነው የአረቡን አለም አብዮት ጅማሮ ተከትሎ መሆኑ ይታወሳል። የአባይ ግንባታ ፕሮጀክት የተጠበቀውን ያክል የህዝቡን ትኩረት ሊስብ አለመቻሉና የህዝቡን ምሬት መጨመሩ አገዛዙን ክፉኛ ያስደነገጠ መሆኑን በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወቃል።

## አሜሪካ ለመለስ ዜናዊ ሽብርተኛ አገዛዝ የምትሰጠውን ድጋፍ እንድታቆም በዋሽንግተን ዲሢና አካባቢዋ ያሉ ኢትዮጵያዊያን በሠላማዊ ሠልፍ ጠየቁ

በምዕራባዊያን የገንዘብና የፖለቲካ ድጋፍ ህዝባችንን አፍኖና ረግጦ እየገዛ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዜጎቻችን ላይ አጠናክሮ የቀጠለውን እስር በማውገዝ ቁጥራቸው በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በትናንትናው ዕለት በአሜሪካን ስቴት ዲፓርትሜንት ፊት ለፊት ተገኝተው ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ ማካሄዳቸውን ሪፖርተራችን ከሥፍራው በላከልን ዜና ገለጸ።

ሞት ለወያኔ-፤ ሞት ለጎጠኞች ፤ ሞት ለሽብርተኛው መለስ ዜናዊ፤ መለስ ዜናዊ ለፍርድ ይቅረብ፤ አሜሪካ ለፋሽስቱ መለስ ዜናዊ የምታደርጊውን እርዳታ እንቃወማለን፤ የቱኒዚያን፤ የግብጽና የሊቢያን ህዝብ ነጻ ያወጣው ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ይደገማል፤ ወዘተ የሚሉ መፈክሮችን በከፈተኛ ቁጭትና እልህ ሲስተጋቡ እንደነበረ የገለጸው ዘጋቢያችን በሰላማዊ ሰልፉ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ለወያኔ ያላቸው ትዕግሥት የተሟጠጠ እንደነበር ያስተጋቡ ከነበረው መፈክር መረዳት ይቻላል ብሎአል።

ሰላማዊ ሰልፉን ያስተባበረው በሰሜን አሜሪካ የፖለቲካና ሲቪክ ድርጅቶች ጥምረት የሆነው ድርጅት በአጭር ጊዜ በተዘጋጀው በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተገኙት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እጅግ እንዳስደሰተው በመግለጽ ወያኔ በህዝባችን ላይ የሚፈጽመው ሽብር እስኪገታ ድረስ ተመሳሳይ ተቃውሞ ሰልፎችንና ህዝባዊ ስብሰባዎችን በማካሄድ በአገራችን የሚካሄደውን ፋሽስታዊ እርምጃ ማጋለጡን እንቀጥላለን ብሎአል።

ይህ በዚህ እንዳለ በአውስትራሊያ አገር በሜልቦርን ከተማ የሚገኝ “ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ የድጋፍ ኮሚቴ የተባለ ድርጅት “መለስ ዜናዊ አገዛዝ በንጽኋን ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን የእስርና የአፈና እንግልት ለመቃወም ባለፈው ቅዳሜ መስከረም 15 ቀን በሜልቦርን ከተማ የጠራው ህዝባዊ ስብሰባ በጋለ ስሜት መካሄዱን የደረሰን ዜና አመለከተ።

የስብሰባው ተሳታፊዎች ዘረኛው የመለስ አገዛዝ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ስላለው የሰብአዊ መብት ጥሰት በሰፊው ከተወያዩ በኋላ ህወሀት/ ኢህአዴግ በቅርቡ በግፍ ያሰራቸውን እነ አቶ እስክንድር ነጋ፤አንዱአለም አራጌ፤ ዘመኑ ሞላ፤አሳምነው ብርሃኑ፤ ናትናኤል መኮንን፤ በቀለ ገርባ ፤ ኦልባና ሌሊሳ፤ ደበበ እሸቱ፤ እንዲሁም ሌሎች ጋዜጠኞች፤ ታዋቂ ሰዎች እና የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ የአለማቀፍ መንግስታትን ጠይቀዋል።

በመጨረሻም ተሳታፊዎቹ በእስር ላይ ለሚገኙት ዜጎች ቤተሰቦች የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ህብረተሰቡን በማስተባበር ለማሰባሰብ በሙሉ ድምጽ ሲወስኑ ይህንንም የሚያከናውኑ ልዩልዩ ንኡሳን ኮሚቴዎችን ማዋቀራቸውን የደረሰን ዜና አክሎ አመልክቷል።

# የመለስ አገዛዝ ሰድቦ ለሰዳቢ ሰጠን

በአለፈው 2003 መጨረሻ አካባቢ የብርታኒያ የዜና አውታር (ቢቢሲ) የምርመራ ጋዜጠኞቹን በስውር ወደ ኢትዮጵያ ልኮ እንደነበር ይታወሳል። ጋዜጠኞቹ በኦጋዴን፣ በባሌ፣ በወላይታ፣ በደቡብና ምዕራብ ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ በመዘዋወር ከታዘቡት ውስጥ ጥቂቱን በነሐሴ ወር ለዓለም ህዝብ አሳይተዋል።

በዚያም ጊዜ ባቀረቡት ዘገባ መሠረትም

- የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታን ሳይጨምር ለልማት እየተባለ ከምዕራባዊያን በየዓመቱ የሚጎርፈው 3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለትም አምሳ አራት ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር (ብር 54, 000, 000, 000) መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ እንደፈለጉ እንደሚያዙበት ማረጋገጣቸው፤
- መለስን አልደገፉም የተባሉ ነዋሪዎች መሰረታዊ የሆኑ የምግብና የውሃ አቅርቦት እርዳታ መነፈጋቸውና በዚህም ምክንያት አዋቂዎች ሳይቀር በረሃብ መሞት መጀመራቸው ቦታው ድረስ በመሄድ በዓይኖቻቸው መመልከታቸውን፤
- መለስን ያልደገፉ ገበሬዎች ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር እንደማያገኙ ከገበሬዎቹ አንደበት መስማታቸው፤
- ወጣት ሴቶች ብቻ ሳይሆን በእድሜ የገፉ እናቶች፣ አያቶች፣ ነፍሰጡሮች ሳይቀር በወታደሮች መደፈራቸውን ከበደሉና ግፉ ቀማሾች አንደበት መስማታቸውና የተበዳዮችን ጠባሳዎች መመልከታቸው።
- ሰቆቃ የተፈፀመባቸው፤ ተዘቅዝቀው የተሰቀሉ፣ ብልታቸውን የተኮላሹ ወንዶችን ማናጋገራቸው፤
- በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስማት የሚሰቀጥጡ ግፎች የሚፈፀሙ መሆኑ

በምስል በተደገፉ ማስረጃዎች አረጋግጠዋል።

ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የቢቢሲን ዘገባ ማፍረሻ ያለውን የተለመደውን ድራማ ሰርቶ ሲያደነቁረን ከረመ። ለጋዜጠኞቹ መረጃ የሰጡትን፤ በአስተርጓሚነት የአገለገሉትን ለቃቅሞ አሰረ፤ አንገላታ።

ይሁን እንጂ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰቆቃ (ቶርቸር) እንደሚፈጽም እና የእርዳታ እህል ለፓለቲካ ተግባር እንደሚያውል አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ እንደሚያውቅ ዊኪሊክስ ከቢቢሲ ዘገባ በኋላ ይፋ ያደረጋቸው ሾልከው የወጡ መረጃዎች አረጋገጡ።

ቢቢሲ እነዚህን ተጨማሪ ነገሮችን ይዞ እንደገና ቀረበ። የአገሪቱ የውጭ ትብብር ሚኒስትር የሆኑትን ሚስተር አንድሬ ሚቸልን "ለእንዲህ ዓይነቱ መንግሥት እንኳንስ በመቶዎች ሚሊዮኖች እንዴት አንድ ፓውንድ እንኳን ይሰጣል?" ሲል ሞገተ።

በዚህ አጭር ሙግት ውስጥ ኢትዮጵያዊያንን ሊያሳስቡ የሚገቡ በርካታ ነገሮች ተሰምተዋል፤ ከትንሹ ጀምረን ወደ ትልቁ እንሂድ:

1. ተጠሪነቱ ለሚስተር አንድሬይ ሚሸል የሆነ የልማት ድርጅት በኢትዮጵያ ያለውን የእርዳታ አሰጣጥ ሥርዓት መርምሮ "በተቀናጀ መንገድ የእርዳታ እህል ለሌላ ተግባር እንደማይውል አረጋግጧል" አሉ። "የድርጅትዎ መርማሪዎች ገጠር ድረስ ሂደው መርምረዋል ወይ?" ተብለው ሲጠየቁም "አዎ ተቀማጭነታቸው እዛው ነው" አሉ። ሆኖም የልማት ሠራተኞቹ ምርመራውን ያካሄደቱ አዲስ አበባ ውስጥ ቁጭ እንደሆነ ቢቢሲ ሠራተኞቹን ጠይቆ ማረጋገጡ በፐሮግራሙ መዝጊያ ላይ አሳወቀ።
2. ሚኒስትሩ "የእንግሊዝ የእርዳታ ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና አይገባም። ከ1997 ወዲህ በቀጥታ መንግሥትን መደጎም ትተናል። እርዳታችንን በቀጥታ ለክልሎች ነው የምንሰጠው" ሲሉ ተሟገቱ - ከወሬ ባለፈ ክልሎች ያሉ ይመስል። ሁሉም-ጠቅላይ በሆነ አገዛዝ ውስጥ ገንዘብ ለማዕከል ተሰጠ ለክልል አሊያም ለወረዳ እምብዛም ለውጥ የሌለው መሆኑ እርሳቸው ያጡታል ብለን አናምንም።
3. ሚኒስትሩ "በእንግሊዝ እርዳታ በኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ እጥረትን በግማሽ (50%) ቀንሰናል" አሉ። መለስ አመጣሁ እያለ የሚመፃደቅበት እድገት የእንግሊዝ እርዳታ ውጤት መሆኑ መናገራቸው መልካም ቢሆንም የሰጡትን ቁጥር ግን እንጠራጠራለን። እውን ኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ እጥረት በግማሽ ቀንሷል? በምንስ ጋር ነው የተነፃፀረው?
4. ከሁሉም አስከፊው ግን ምርጫን በሚመለከት የተናገሩት ነው። መለስ ዜናዊ 99.6% አሸንፍኩ ያለበት ምርጫ "ገለልተኛ ቡድን እንደገመገመው ምርጫው ፍጹም ነው ባይባልም እንኳን በአፍሪቃ ደረጃ ጥሩ ነበር፤ ከበፊተኛው ምርጫም የተሻለ ነበር" አሉ።

ሁሉም የሚኒስትሩ ምላሾች የሚያሳዝኑና የሚያስተዛዝቡ ቢሆንም የመጨረሻው ግን የሚያበግን ነው።

ለመሆኑ የአፍሪቃ ዲሞክራሲ መመዘኛ የተለየው በምን ምክንያት ነው? እንዲህ አሳንሰው የሚያይዋት አፍሪቃ ሰሜን አፍሪቃንም ይጨምራል ወይስ የጥቁርን ዘር ብቻ ነው? እንደምን የ2002ቱ "ምርጫ" ከ1997ቱ የተሻለ ነበር ይባላል። እነማናቸው እንዲህ ያሉት "ገለልተኞቹ" ገምጋሚዎች?

እንደሚታወቀው መለስ ዜናዊ የእርዳታ ጥገኛና ሱሰኛ ነው። በረሃ እያለ በአሸዋ የተሞሉ ጆንያዎችን ስንዴ ነው እያለ ሸጦ ባጋበሰው ገንዘብ እዚህ ደርሷል። አሁንም ነብሱ ያለችው በእርዳታ ነው። ከእርዳታ የዘረፈውንም የሚያስቀምጠው በእነዚሁ በለጋሾቹ አገር ነው። ይህንን ሁሉ የሚያውቅ ለጋሽ እንደምን ያከብረን?

መልዕክቱም ግልጽ ሆኖ፤ ጠልቆ ሊሰማን ይገባል። "ራሱን ያቀለለ አሞሌ ባለእዳ አይቀበለውም" እንዲሉ በራሳችን ባርያ ፈንጋዮች እየተገረፍን እንደምን ባዕዳን ሊያከብሩን ኖሯል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ራሱ የሚያደርስብን በደል ሳያንስ በዓለም አደባባዮችን ምን ያህል እንደተናቅንና እንደተዋረድን በየእለቱ የምናየው ሃቅ ሆኗል። ከዚህም አልፎ እነሆ የመንግሥታት ሹማምንትም ይፋዊ መግለጫ እየሆነ ነው? ምንድነው የምጠብቀው? እስከመቼ በመለስ አገዛዝ ክብራችን እንደዋረደ እንቆያለን? መለስ ሰድቦ ለሰዳቢ፤ ገርፎ ለገራፊ እንዲያቀብለን እንፈቅዳለንን? ወይስ መለስን ራሱን ከጫንቃችን አውርደን ክብራችንን እንቀዳጃለን? ምርጫው የእያንዳንዳችን ነው።

በግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ውስጥ የተሰባሰብን ኢትዮጵያዊያን "በቃን!!!!" ብለናል። እርስዎስ?

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

## ለመስከረም 21 ሰላማዊ ሠልፍ በመጥራታቸው ከታሰሩት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዳኛዋ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ፈቃድ ሳታገኙ ለምን ወረቀት ማባዛት ውስጥ ገባችሁ በማለት ላቀረበቺው ጥያቄ ፣ አቶ ክንፈ ሚካኤል በድፍረት በህገ መንግስቱ መሰረት አንድ ሰለማዊ ሰልፍ በ48 ሰአታት ውስጥ ፈቃድ ካልተሰጠው እንደተፈቀደ ይቆጠራል፣ እኛም በተደጋጋሚ ወደ ከንቲባው ኩማ ደመቅሳ ብንሄድም መልስ ሊሰጠን አልቻለም፣ ስለዚህ ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት ሰለማዊ ሰልፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምረናል በማለት መመለሳቸው ታውቆአል።

አቃቢ ህግ ከውጭ አገር ገንዘብ ተቀብለዋል ለሚለው ክስ አቶ ክንፈ ሚካኤል ሲመልሱ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ፓርቲ በራሱ ገንዘብ አይንቀሳቀስም፣ ፓርቲዎቹ ደሀ ናቸው ስለዚህ ከኢትዮጵያውያኑ ገንዘብ መቀበል የተለመደ ነው፣ እንኳንስ እኛ ኢህአዴግም ገንዘብ ይቀበላል በማለት አገዛዙን አንገት የሚያስደፋ ምላሽ ሰጥተዋል።

አቶ ክንፈ ሚካኤል፣ ሌሎች እስረኞች በማያዉቁት ጉዳይ መታሰራቸውን ገልጸው፣ እነርሱ እንዲፈቱና እርሳቸው ሀላፊነቱን እንዲወስዱ ፍርድ ቤት ተብዬውን ጠይቀዋል። ከዚያ በሃላ እንደተለመደው እስረኞቹን ለማሰቃየት ሌላ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቶ የ ዕለቱ የፍርድ ቤት ድራማ ተተናቆአል።

በወያኔ የሰሞኑ ዘመቻ በሽብር ተጠርጥረው የተያዙት ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች በመላ አሰቃቂ የሆነ ድብደባ ሳይፈጸምባቸው እንዳልቀረ የደረሱን መረጃዎች አመልክተዋል።

## በስዊድን የሚገኙ አትዮጵያውያን የተቃውሞ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በስዊድን የኢትዮጵያ ማህበር ተወካይ የሆኑት አቶ ግሩምጌታ ዘላለም እንዲህ አይነቱን የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ የተፈለገው የታሰሩ ፖለቲከኖችና ጋዜጠኞች እንዲፈቱ ለመጠየቅ ነው በማለት በአገራችን ፍትህ እስኪከበር ና ዜጎች የአገራቸው ባለቤት መሆን እስኪችሉ ድረስ ኢትዮጵያዊያኑ ጸንተው መታገል እንዲችሉ ጥሪ አቅርበዋል።

በሰላምዊ ሰልፉ ላይ በስዊድን የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ኮሚቴ ሰብሰቢ ንግግር እንዳደረጉና ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለሰላማዊ ሰልፈኞቹ የላከው የጽሁፍ መልዕክት በንባብ መሰማቱ ተያይዞ በደረሰን ዜና ተመልክቶአል።

በመጨረሻም ሰልፈኞቹ ለሲዊድን ፓርላማና የውጪ ጉዳይ ሚንስትር የጻፉት ማመልከቻ በሰልፉ ተወካዮች አማካይነት ለማለስልጣናቱ መሰጠቱ ታውቆአል።

## ሂውማን ራይትስ ወች የእንግሊዙን የልማት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሂውማን ራይተስ ወች፣ ገለልተኛ የመንግስት አካል እርዳታውን እንደሚቆጣጠረው ተደርጎ በአንድሪው ሚቸል የቀረበው አስተያየት ተገቢ ያልሆነና ፍጹም አሳሳች ነው።

ለኢትዮጵያ ከሚሰጠው እርዳታ ውስጥ እጅግ በጣም ትንሹ ለምግብ እርዳታ ተብሎ የሚሰጠው መሆኑንና ይህም እርዳታ ችግር እንዳለበት አንድሪው ሚቸል መናገራቸው ተገቢ አለመሆኑን የገለጠው ሂውማን ራይተስ ወች፣ ከ7 ሚሊዮን በላይ ህዝብ በሴፍቲ ኔት ወይም በመጠባበቂያ ምግብ እርዳታ፣ ከ7-10 ሚሊዮን የሚሆነው ህዝብ ደግሞ በአስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚኖር በመሆኑ እርዳታውን አሳንሶ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም ብሎአል። እንደ ሂውማን ራይተስ ገለጻ 20 በመቶ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ በአንድም ይሁን በሌላ በውጭ እርዳታ የሚኖር ነው።

ሂውማን ራይተስ ወች የኢትዮጵያ መንግስት በአገሩ ምንም አይነት ምርመራ እንዲካሄድ እንደማይፈልግ የታወቀ ቢሆንም፣ እንግሊዝም ሆኑ ሌሎች መንግስታት ከግብር ከፋዩ ህዝባቸው የሚሰበስቡትን ገንዘብ እንዴት ሊቆጣጠሩት እንደሚገባ ከኢትዮጵያ መንግስት መመሪያ ሊቀበሉ አይገባም ብሎአል።

እንግሊዝን ጨምሮ ሁሉም አገሮች ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጡት እርዳታ ህዝቡን ለመጨቆኛ እየዋለ አለመሆኑን ማረገጋጥ ይጠበቅባቸዋል ሲል አክሎአል።

ሂውማን ራይተስ ወች በመጨረሻም የእንግሊዝ መንግስት ወደ ገጠር ወርዶ በሂዋማን ራይተስ ወችና በቢቢሲ የቀረበውን ዘገባ ማጣራት ይጠበቅበታል ብሎአል።

## አሸባሪው፣ ዘረኛና አምባገነን የወያኔ . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

መድረክ በመግለጫው ሁሉም የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤ የሁሉም የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች ሰብዓዊ-መብት መከበሩ በአስቸኳይ እንዲረጋገጥ፤ በፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ ስም የሚደረገው የህዝብ መብት ረገጣና እስራት በአስቸኳይ እንዲቆም፤ ህዝብን አፍኖ ለመግዛት ታስቦ የተዘጋጀው "የፀረ-ሽብርተኝነት" አዋጅ ከበርካታ የሕገ-መንግሥቱ አንቀፆች ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ጊዜ ሳይሰጠው እንዲሻር፤ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በወንጀል ተጠርጥሮ እስካልተፈረደበት ድረስ እንደወንጀለኛ ያለመታየት ሕገ-መንግሥታዊ መብት እንዳለው ይታወቃል። በመሆኑም የመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን ፍርድ ባልተሰጠባቸው ዜጎች ላይ እንደተፈረደባቸው ወንጀለኞች በመቁጠር የሚያሰራጩትን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ በአስቸኳይ እንዲያቆሙ አሳስቧል። በመጨረሻም "በሽብርተኝነት ስም የህዝብ መብቶችን ማፈን ይቁም!" ሲል መድረኩ ያለውን አቋም ገልጿል።

## ረሃብ ጊዜ አይሰጥም
## ወገኖቻችንን ለመታደግ፣ ወያኔን ለማስወገድ እንጣደፍ

የግንቦት7 ርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 75 ላይ ወጥቶ የነበረ

“ለስድስት ተከታታይ ዓመታት ከአስር በመቶ በላይ የኢኮኖሚ እድገት አሳይተናል” የሚለው ዓይን ያወጣ ውሸት፤ “ድህነትን ተረት እናደርጋለን” የሚለው ጉረኛ መፈክር፤ የወያኔዎችና ጀሌዎቻቸው በፎቅና ቪላዎች መንበሽበሽ፤ ለም መሬቶች በአበባ እርሻዎች መተካታቸው እና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ ”የህዳሴ ብስራቶች” ለሕዝባችን ምሳና እራት አልሆኑም።

የረሃቡ ስጋት እየገፋ ሲመጣ መለስ ከአፄ ኃይለሥላሴም ሆነ ከኮሎኔል መንግሥቱ በባሰ ተፈጥሮ ላይ ማላከኩን ተያይዞታል። ለመሆኑ ተፈጥሮ ብቻውን እየተደጋገመ ለሚመጣ ችጋርና ቸነፈር በቂ ምክንያት ሆኖ ያውቃልን? ለምንድነው ፍትህና ነፃነት በሰፈነባቸው አገሮች ውስጥ ዝናብ ጠፍቶ የእርሻ ምርት ቢቀንስ እንኳን ሰው በረሃብ የማይሞተው? አስከፊ የረሃብ ዜናዎች የሚሰማባቸው አገሮች በሙሉ ነፃነት የታፈነባቸው አገሮች መሆናቸውስ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው? የዝናብ እጥረት ለኢትዮጵያዊ ገበሬ አዲስ ነገር አይደለም። ለምንድነው አንድ ዓይነት ችግር እየተደጋገመብን መላ መፈለግ ያቃተን? “ችግር የመሳካት እናት ናት” የሚለው ብሂል ምነው እኛ ዘንድ አልሰራ አለ? የመጨረሻው ጥያቄ መልስ አጭርና ቀጥተኛ ነው። ችግር የመሳካት እናት የምትሆነው በነፃነት ማሰብ የሚችል ጭንቅላት ሲኖር ነው።

በባርነት ጨለማ ውስጥ ያለ ጭንቅላት ለችግሮች መፍትሄ የማፍለቅ አቅም የለውም። እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ድኩም ጭንቅላት ችግሮችን ማሸነፍ ሳይሆን ተሸናፊነትን ተቀብሎ ከችግሮች ጋር ተስማምቶና ተወዳጅቶ መኖርንይመርጣል። ለዚህም ነው የአስተዳደር በደልና ረሃብ ምክንያትና ውጤት ብቻ ሳይሆን እጅና ጓንትም ጭምር የሆኑት። ነፃነት ያለው ሕዝብ ረሃብን እንደሚያሸንፍ ተደጋግሞ የታየ ጉዳይ ነው _ ህንድ የቅርብ ጊዜ ምሳሌያችን ነች። ለዚህም ነው ረሃብን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ውጤት ብቻ አድርጎ ማቅረብ እውነትን መሸፈጥ የሚሆነው። ረሃብ የብልሹ አስተዳደር ውጤት ነው።

በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋው ስር የሰደደ ድህነትና ረሃብም የዘመናት የብልሹ አስተዳደር ውጤቶች ናቸው። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጀምሮ የነበረው ብልሹ የምጣኔ ሃብት አስተዳደር አገዛዝ በተቀየረ ቁጥር እየባሰበት መጥቷል። በረሃብ የሚጠቃው ሕዝብ ብዛትም እንደዚያው እየጨመረ መጥቶ ዛሬ 14 ሚሊዮን ሕዝብ እርዳታ ፈላጊ ሆኗል። ችጋር አድማሱን አስፍቶ ቀድሞ በለምለምነታቸው ብቻ ይታወቁ ወደ ነበሩት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ መንደሮችም ዘልቋል። አገራችንን የረሃብ ቀጠና ካደረጉ የ19 ዓመታት የወያኔ “የዘርፈህ ብላ” የኢኮኖሚ ፓሊሲ ውጤቶች መካከል አንዳንዱን ለአብነት ያህል መዘርዘር ይቻላል።

1. የወያኔ ቁንጮዎች ራሳቸውን ባለሚሊዮኖች አድርገዋል። እነዚህ በአንድ ጀምበር የበቀሉ ቱጃሮች ከገንዘብ በተጨማሪም የጄኔራልነት፣ የሚኒስቴርነት፣ የክልል ገዢነት፣ እጅግ ቢያንስ የቢሮ ኃላፊነት ሥልጣንን ኪሳቸው ውሰጥ ከተዋል። የመንግሥት ሥልጣንና ሃብት ይኸን ያህል የተቆራኙበት ሥርዓት በኢትዮጵያ ኖሮ አያውቅም። የጥቂቶች ያለአገባብና ያለቅጥ መክበር በአንፃሩ ደግሞ የብሃኑን ሕዝብ መደህየት ድህነትን ቀጣይ ያደርጋል።
2. በአቋራጭና በፍጥነት ለመክበር አስተማማኙ መንገድ የገዛ ራስ ጥረትና ታታሪነት ሳይሆን ቅጥፈት፣ አጭበርባሪነትና ሎሌነት ማደር መሆኑን በተግባር ወያኔ እያሳየ ጥሮ ማደርን “ኋላ–ቀር አሠራር” አድርጎታል። በዚህም ምክንያት አድርባይነት፣ ስንፍናና እና ልመና ችግርን የመጋፈጥ አቅማችንን ሰልበውታል።
3. ደኖቻችን ተጨፍጭፈው፣ ለም መሬታችን ተሸርሽሮ በማለቁ የግብርናችን ምርታማነት በእጅጉ ቀነሷል። በዘመነ ወያኔ የደን ጭፍጨፋና የመሬት መሸርሸር በአስደንጋጭ ሁኔታ ጨምሯል። አገሪቷ በፍጥነት ወደ ምድረበዳነት እየተቀየረች ነው።
4. ገበሬና መሬት ተለያይተዋል፤ አዳዲሶቹ ባላሃብቶች ለፈጣን ኪስ መሙላት እንጂ ለዘለቄታ የአፈር ልማት ፍላጎቱም እውቀቱም የላቸውም። ለም መሬቶች በኢንቨስትመንት ስም በዘመኑ የወያኔ ጉልተኞች በመያዛቸውና እነሱ ደግሞ በተራቸው ለባዕዳን እየሸጡ በመሆኑ ባለሃገሩ ጭሰኝነት እንኳን አጥቶ ለቀን ሠራተኝነትና ልመና ተዳርጓል። በዚህም ምክንያት ገበሬው እንኳንስ ትልቁን የአየር መዛባት ትንሿንም የዋጋ ነውጥ መቋቋም እስከማይችልበት ደረጃ ተዳክሟል።
5. በዘር በተመሰረተ ክልላዊ ድንበር ሳቢያ ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች በአገራቸው ውስጥ ተዘዋውረው መሥራት አልቻሉም። ከሰሜን ወደ ደቡብ ከተሰደደ የአገራችን አርሶ አደር ይልቅ ለቻይና ገበሬ መሬት ማግኘት ይቀለዋል። እንዲያውም ኢትዮጵያዊው ገበሬ በዱላ ሲባረር፤ የቻይናው ገበሬ ብድርና ማበረታቻዎች ይሰጠዋል።
6. ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች ድርቅን መቋቋም ስለሚችሉ ሰብሎች ወይም የአስተራረስ ዘዴዎች ማሰብ፣ መመራመርና መፈተሽ አይችሉም። አዲስ ነገር መሞከር የግብርና ፓሊሲን በመቃወም ወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር ነው። ፈጠራ በእንዲህ ዓይነት ሥርዓት ውስጥ ሊያድግም።
7. ፋይዳ ያለው የስነ ሕዝብ ፖሊሲ ባለመኖሩ የሕዝብ ብዛት አሻቅቧል። እንደ ኢኮኖሚው ሁሉ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት ሊቆጣጠር የሚሞክረው ቢሮ ውስጥ ቁጭ ተብሎ በሚደረግ የቁጥር ምርጫ ነው። የስታተስቲክሱ ባለሥልጣን ቁጥራችንን በትክክል ሊነግረን ባይፈልግም እንኳን ረሃብ መብዛታችንን እየነገረን ነው።

እነዚህና የመሳሰሉት ጭብጦችን በማንሳት የረሃቡ መሠረታዊ ምክንያት ወያኔ እንጂ ተፈጥሮ አለመሆኑን አስረግጠን እንናገራለን። ሕዝባችን በነፃነት ማሰብ፣ መመራመር፣ መፈተሽ ቢችል ኖሮ ረሃብን ማጥፊያ ብልሃት ማግኘት ባላቃተውም ነበር። ወደፊትም ቢሆን ተፈጥሮ እኛ እንደፈለግናት አትሆንም፤ መተማመኛችን የሰው ልጅ ወሰን የለሽ የፈጠራ ችሎታና ችግሮችን የመፍታት አቅም ነው። ለዚህ ችግሮችን በልጦ መገኘት ያስፈልጋል። ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሌ ከችግሮች በታች ሆኖ የእሱን ፈቃድ እንዲያሟላ ይፈልጋል፤ ለዚህም ነው ባርነትን ያወጀብን። እኛ ደግሞ የችግሮቻችን ቁንጮ ራሱ ወያኔ ነው የምንለው ለዚህ ነው። ወያኔን ሳናስወግድ ድህነትንና ረሃብ እናስወግዳለን ማለት ዘበት ነው።

ድህነት የወያኔ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ስለመሆኑ በዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ያነሳነው ጉዳይ ነው። ረሃብና ችጋርም እንደዚያው የወያኔ “ጪስ አልባ” እንዱስትሪዎች ናቸው። ሕዝባችን ተራበ ማለት የወያኔ ኩባንያዎች ሥራ አገኙ ማለት ነው። ወያኔ የራሱን “መንግሥታዊ ያልሆኑ” ድርጅቶች የማጠናከርና ገለልተኞቹን የማቀጨጭ ሥራ የጀመረው አራት ኪሎ እንደደረሰ ቢሆንም ረሃቡ በጨመረ መጠን እሱም “ገበያውን” ብቻውን ለመቆጣጠር የሚያደረገው ልብ ይሏል።

ረሃብ ያለፉት ሶስት ተከታታይ አገዛዞች የባህሪይ ተመሳሳይነትንም አጉልቶ አሳይቶናል። የሶስቱም አገዛዞች ቁንጮዎች ሰለረሃብ ተጠይቀው የሰጡት ትዕቢት የተሞላበት ምላሽ በሚገርም መጠን ተመሳሳይ ቢሆኑም የመለስ ግን ከሁሉ ይብሳል። መለስ ከቀደሙት ሁለቱ በባሰ እየለመነ ይሳደባል፤ እየተሳደበ ይለምናል። ስለ ኢኮኖሚ እድገት ሰፊ ገለፃ ከሰጠ በኋላ ንግግሩን በእርዳታ ልመና ይደመድማል። በመለስ አመክኖ ተፈጥሮ፣ ለጋሽ አገራት፣ የእርዳታ ድርጅቶች እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለረሃቡ ተጠያቂ ናቸው። እውነታው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ለወገኖቻቸን መራብ ተጠያቂው ወያኔ ነው። ወያኔን ሳናስወግድ ድህነትና ረሃብን ከኢትዮጵያ ምድር መንቀል አንችልም።

በወያኔ አገዛዘ በረሃብ ለሚጠቃው ወገናችን መድረስ የምንችለው፤ የረሃቡን መሠረታዊ ምክንያት የሆነውን የወያኔን አገዛዝ አስወግደን ፍትህና ነፃነት የሰፈነባትን፤ ፈጠራ የተስፋፋባትን ኢትዮጵያን ስንገነባ ብቻ ነው። ጊዜ የለም .... **ረ ሃ ብ ጊ ዜ አ ይ ሰ ጥ ም** ። የወገኖቻቸንን ሕይወት ለመታደግ በአንድነት እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አሸባሪው፣ ዘረኛና አምባገነን የወያኔ አገዛዝ በሽብርተኝነት ስም እየፈጸመ ያለው የጅምላ እስራት ስርአቱ የራሱን መቀበሪያ ጉድጉአድ እየቆፈረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ንጹሃን ዜጎችን ሽብርተኞች ናችሁ በማለት የጀመረው የጅምላ እስራት፣ የአምባገነኑ ስርአት ማብቂያ ዋዜማ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን አገዛዙ እየፈጸመ ያለው ድርጊት ደግሞ የራሱን መቀበሪያ ጉድጉአድ እየቆፈረ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው በማለት በርካታ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለዘጋቢያችን ገለጹ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርትና በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች በመዘዋወርም ያነጋገራቸው በርካታ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እንደገለጹት የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ የሚፈልገውን ግፍ ሁሉ ፈጸመ፣ ኢትዮጵያዊያንን በርሃብ አለንጋ ቀጣ፣ ለሞትና ለስደት ዳረገ። ይህ ሁሉ አላረካው ሲል ደግሞ ለኢትዮጵያ አንድነትና እድገት እንቅልፍ አጥተው እየሰሩ ያሉ ንጹህና ውድ ኢትዮጵያዊያንን ተራ በተራ ወደ ቃሊቲና ሌሎች በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች የሚገኙ እስር ቤቶች ሽብርተኞች ናችሁ እያለ አጎረ። ይህን ሁሉ እየፈጸመ ያለው ቀደም ብሎ በኢትዮጵያዊያን ላይ የፈለገውን በደል ሲፈጽምና የፈለገውን እንዳሻው ሲያደርግ ኢትዮጵያዊያኑ ቁጣቸው ባለመቀስቀሱ የት ትደርሳላችሁ በሚል ንቀት እንደሆነ ገልጸው አሁን የጀመረው ዘመቻ ግን እጅግ በርካቶችን ያበሳጨ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንም በያዝነው አመት ወያኔን ፍጹም በሆነ ወኔ እንዲፋለሙ ያዘጋጀ ነው። እናም እየፈጸመ ያለው ድርጊት ደግሞ የራሱን መቀበሪያ ጉድጉአድ እየቆፈረ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አቶ አንዱአለም አራጌ፣ የኦፌዴን ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት አቶ በቀለ ገርባ፣ የኦህኮ የጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አልባና ሌሊሳ፣ የአንድነት ፓርቲ ብሔራዊ ምክር ቤት አባል የሆኑት አቶ ናትናኤል መኮንንና አቶ አሳምነው ብርሀኑ፣ ታዋቂው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ጋዜጠኛ ውብሸት ታየ፣ ጋዜጠኛ ርዮት ዓለሙ፣ ጋዜጠኛ ስለሽ ሐጎስ እንዲሁም አርቲስት ደበበ እሸቱ የአምባገነናዊው ዘረኛ ሥርዓት ጅምላ እስራት ሰለባ ከሆኑት ጥቂቶቹ መሆናቸው በተለያዩ የዜና አውታሮች ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

ይህ በንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ባለፈው ቅዳሜ በቅርቡ በ”ሽብርተኝነት” ስም እየታሰሩ ያሉትንና በሠላማዊ ትግልና በጋዜጠኝነት እየሠሩ ያሉትን ግለሰቦች አስመልክቶ ”በሽብርተኝነት ስም የህዝብ መብቶችን ማፈን ይቁም!” በሚል ርዕስ መግለጫ አውጥቷል። መድረክ በመግለጫው ታሳሪዎቹ በሀገሪቱ በሚደረገው ፈታኝ ሠላማዊ ትግል ውስጥ በሕገ-መንግሥቱ ጥላ ስር ግንባር ቀደም ተዋናይ የሆኑ ፖለቲከኞችና ሞያዊ ግዴታቸውን አክብረው ለህዝብ ትክክለኛና ያልተዛባ መረጃ ለማድረስ የሚተጉ ጋዜጠኞች መሆናቸውን መድረክ አጥብቆ እንደሚያምን ገልጿል። በማያያዝም ወያኔ ኢህአዴግ በሽብርተኝነት ወንጀል ስለመታሰራቸው በመገናኛ ብዙኀን ፕሮፖጋንዳ ሲያሰራጭ እንጂ ስለፈፀሙት የሽብር ተግባር ተጨባጭ ማስረጃ ሲያቀርብ አለመታየቱን መድረክ ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ በወገኖቻችን ላይ እየፈጸመ የሚገኘውን ሽብር በመቃወም በየሃገሩ ሰላማዊ ሰልፍ እያዘጋጁ መሆኑ ታወቀ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በወገኖቻችን ላይ የጀመረውን የእሥር ዘመቻ ለማስቆምና ሽብርተኝነትን በመከላከል ሥም በአገዛዙ እየተካሄደ ያለውን መንግሥታዊ ሽብር ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ለማሳወቅ ኢትዮጵያዊያኑ በየሚኖሩበት የምዕራብ አገሮች ከፍተኛ የሆነ እንቅስቃሴ እያካሄዱ መሆኑን ወደ ዝግጅት ክፍላችን እየደረሱ ያሉ መረጃዎች አመለከቱ።

ባለፈው ሰኞ በአሜሪካን አገር ስቴት ዲፓርትመንት ፊት ለፊት የተጀመረው የኢትዮጵያዊያን ተቃውሞ፤ በነገው ዕለት መስከረም 19 ወይም እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ስብተምበር 30 በስዊድን ስቶክሆልም እንዲሁም ከወያኔ አገዛዝ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባላት የእንግሊዝ ዋና ከተማ ሎንዶን የፊታችን እሁድ መስከረም 21 ወይም አክቶበር 2 እንደሚደረግ ለማወቅ ተችሎአል።

ከዚህ በተጨማሪም በሰሜን አሜሪካ፤ በአውስትራሊያና በአውሮጳ የተለያዩ ከተሞች ተመሳሳይ የሆነ የተቃውሞ ሰልፍ እየተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ የየአገሮቹ መንግሥታት ወያኔ በጸረ ሽብርተኝነት ዘመቻ ሥም ህዝባዊ ተቃውሞን ለመደፍጠጥ በወገኖቻችን ላይ እየፈጸም ያለውን እስር፤ ግርፋትና ግዲያ እንዲገነዘቡ ለማስቻል ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ በተጓዳኝ እየተካሄደ መሆኑ ታውቆአል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባለፈው ሰኞ ከአሜሪካን አገር ስቴት ዲፓርትመንት ፊት ለፊት በተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ንግግር ያደረጉት የዲሞክራሲ አክቲቪስት ታማኝ በየነ፤ የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አባል አቶ ኤፍረም ማሉቦና ወጣቶችን በመወከል ንግግር ያደረገች አንዲት ሴት ታጋይ የወያኔ የመከራና የግፍ አገዛዝ እንዲያበቃ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ላሉ ኢትዮጵያዊያን ጥሪ ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሎአል። አርቲስት ታማኝ በየነ ባደረገው ንግግር አገራችንን ለመበታተን ታላቅ አደጋ የጋረጠውን የወያኔ አገዛዝ ከሥልጣን ለማውረድ በሚደረገው ትግል ውስጥ ህዝባችንን ቀስፎ የያዘው የፍርሃት መንፈስ ይገረሰስ ዘንድ ሁሉም በራሱ ላይ ዘመቻ መክፈት እንዳለበት አስታውቆአል። አገር ውስጥ ያሉ የዲሞክራሲ ታጋዮች በወያኔ እስር ቤት የሚፈጸምባቸውን ሰቆቃ ከመጠፍ ሳይቆጥሩ እየተጋፈጡ ባሉበት ፤ እነ እስክንድር ነጋና አንዱአለም አራጌን የመሳሰሉ እምነታቸውን በአደባባይ እየተናገሩ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በተለይ በውጪ የምንገኘው ኢትዮጵያዊያን ለወያኔ ማስፈራሪያና ዛቻ ቦታ መስጠት እንደማይኖርበን ተናግሮአል።

የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት አቶ ኤፍሬም ማዴቦ በበኩላቸው ህጻን ከሽማግሌ ሳይለይ በህዝባችን ላይ ሰቆቃ እየፈጸመ ያለው ይህ ዘረኛ አገዛዝ በአስቸኳይ ካልተወገደ በቀር መዘዙ የከፋ መሆኑን ለማስረዳት፤ ድህረ ምርጫ 97 ወላጆቹ በተፈጸመባቸው እስር ምክንያት እስር ቤት የተወለደው የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና ሰርካለም ፋሲካ የ5 አመት ህጻን ልጅ፤ የአባቱ አሳሪዎች የብረት ካቴና እጁ ላይ ሲያስገቡ ምርር ብሎ ሲያለቅስ ርህራሄ የሌላቸው የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ፖሊሶችና ፊልም ቀራጮች እንደመዝናኛ ፊልም ተረጋግተው የቀረጻ ተግባራቸውንና የጭካኔ ድርጊታቸውን ሲፈጽሙ መታየታቸው ሊኖረው የሚችለውን መልዕክት ምን እንደሆነ ሁሉም ልብ ሊለው እንደሚገባ ካስገነዘቡ ቡኋላ ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት የምንችለው እያንዳንዳችን እስከ ህይወት የሚደርስ መስዋ ዕትነት ለመክፈል ስንችል ብቻ መሆኑን አስገንዝበዋል።

## "ልጄ እንደ አባቱ የነፃነት ታጋይ እንዲሆን ነው የምፈልገው"ስትል ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል መግለጿ ተዘገበ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በድህረ ምርጫ 97 የቅንጅት መሪዎችን፤ ጋዜጠኞችንና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን እስር ቤት ባጎረበት ወቅት፤ ዳግም ለወያኔ እስር በተዳረገው ባለቤቷ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር እስር ቤት እየማቀቀች የተገላገለቺው ህጻን ልጇ እንደ አባቱ የነጻነት ታጋይ እንዲሆን ምኞቷ መሆኑን ጋዜጠኛ ስርካለም ፋሲል አዲስ ጉዳይ በተባለ መጽሄት ላይ ባሳተመቺው ጽሁፍ መግለጿን ለማወቅ ተችሎአል።

ጋዘጠኛ ስርካለም በአመዛኙ ስለ ባለቤቷ እስክንድር ነጋ ማንነት በገለፀችበት በዚህ ፅሁፏ ባለቤቴን "ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ታውቁታላችሁ።ከቅርብ ቀናት ወዲህ የመንግስት ሰዎች እስክንድር የሚባል ጋዜጠኛ አናውቅም ቢሉም እናንተ ግን ታውቁታላችሁ"በማለት ነበር ጽህፏን የጀመረቺው።

ይሁንና "አናውቅህም"ያሉት ወገኖቹም በበሳልና በደፋር ጋዜጠኝነቱ እንደሚያውቁት እርግጠኛ መሆኗን ሰርካለም ተናግራለች።

እስክንድር ለሰባት ጊዜ ፍርድ ቤት ቀርቦ አንድም ጊዜ መረጃ ሳይገኝበት በነፃ መለቀቁን፤ እንዲሁም ምርጫ 97ትን ተከትሎ የቅንጅት ምክር ቤት አባል ነህ ተብሎ ከተመሰረተበት ክስ በነፃ መሰናበቱን ያስታወሰችው ጋዜጠኛ ሰርካለም፤ የእስክንድር ብዕር መነሻውና መድረሻው እውነት ብቻ እንደሆነ አመልክታለች።

ባለቤቱ ከመሆኗ ጀምሮ በብዙ ምክንያቶች ስለ እስክንድር ስብዕና ለመናገር እንደምትቸገር የተናገረችው ሰርካለም፤" ይሁንና ስለ እስክንድ ለመናገር ማስረጃ ማሰባሰብ እንደማያሻ፤ የ እስክንድር ጉዳይ ነጻ ለሆኑ ግለሰቦች ቀርቶ በወንጀለኛነቱ ሊዳኘው ላሰፈሰፋው ፍርድ ቤትም ግልፅ የሆነ ነገር መሆኑን ገልፃለች።

"ሆኖም እስክንድር ዕድለኛ አይመስለኝም። የመረጠው መንገድ ለእርሱም ሆነ ለእኛ ለቤተሰቦቹ አደገኛ ነው፤ እነዚህ ሁሉ እስሮች ወቅት እየጠበቁ እንደሚመጡበት ጠንቅቆ ያውቃል" ያለችው ሰርካለም፡- "በኔ እምነት እስክንድር ያላወቀውና የተታለለበት ጊዜ የሚመስለኝ፤ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በኢትዮጵያ ተከብሯል" ሲባል፤ የተማረባትንና በምቾት የኖረባትን አሜሪካን ትቶ ወደሚወዳት አገሩ ተመልሶ" ኢትኦጲስ"ጋዜጣን ሲጀምር " መሆኑን ጠቅሳለች።

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ "ሽብርተኛ" በሚል ስም በመጠራቱ ከልቧ ማዘኗን የጠቀሰችው ሰርካለም፤" ይሁንና "ሽብርተኛ" ያለው በብዕሩ የሚታገልለት የኢትዮጵያ ህዝብ ባለመሆኑ እጽናናለሁ" ብላለች።

ከመታሰሩ ከወራት በፊት የፌዴራል ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነር ቢሮው ድረስ አስጠርቶት "እርምጃ እንወስድብህለን" ብሎ ዝቶበት እንደነበር ያስታወሰችው ሰርካለም፤" እርምጃ እንወስድብሀለን የሚለውን አባባል እስክንድር ህዝብን ላለማስቆጣት በሚል ለዘብ አድርጎ የፃፈው ነው እንጂ፤ ያሉት እንደዛ አይደለም። ያሉትን ለኔ ነግሮኛል። ያን ቃል እስክንድርና ሀላፊው ያውቁታል። ምንም እንኳ እስክንድር ያመነበትን ከመግለፅ ወደ ሁዋላ ባይልም፤ ሀላፊው የተናገረውን ቃል በቃል ያልፃፈው ፈርቶ ወይም ችግር ይፈጠርብኛል ብሎ ሰግቶ አይደለም።ይልቁንም የተባለውን ነገር እንዳለ ቢፅፈው በህዝቦች መካከል አመፅ ሊያስነሳ፤ ዓመፅ ባያስነሳ እንኳ ቂም ይፈጥራል" በሚል ሀሳብ ነው ያልፃፈው ብላለች።

እስክንድርን ለዘብ እንዲል ብታስገድደውም ሆነ ብትለምነው ከዓለማው ልትመልሰው እንደማትችል የገለፀችው ጋዜጠኛ ሰርካለም፤ እንኳን አድጎና ትልቅ ሰው ሆኖ በፍቅር ያገኘሁት ሚስቱ ቀርቶ አንድ እሱን ብቻ የወለዱት እናቱም በቻሉት ሁሉ ሲለምኑት፤ ከቤት ሲጠፋባቸው በየጋዜጣ ቢሮዎች እየሄዱ፡- "ልጆች እስክንድርን አይታችሁታል?" እያሉ ሲያስሱና ደጋግመው ሲማፀኑት መቆየታቸውን፤ ሆኖም ከዓላማው ሊያቆሙ እንዳልቻሉ አስታውሳለች።

"እስክንድር እኔንም፤እናቱንም ባይሰማ እንኳን እሱ ለእናቱ አንድ እንደሆነ ሁሉ፤ለእኔና ለእሱ አንድ የሆነውን የ 5 ዓመት ህፃን ልጁ ናፍቆት በደመ-ነፍስ መማፀኑ ሊሰማው ይገባ ነበር"ያለችው ጋዜጠኛ ሰርካለም፤በመንፈሱ፡-" አባባ፤ ለምን እንደ ሰው ሁሉ እርፍ ብለህ ተቀምጠህ አታሳድገኝም?"እንደሚለው ማሰቡ አልቀረም። ይህ ስለሚሰማውም ይመስለኛል የ 5 ዓመት ልጁን አቅፎ እያሻሸው ልክ እንደ ትልቅ ሰው ሲያናግረው እሰማ ነበር"ብላለች።

በተደጋጋሚ፡- "ናፍቆቴ እወድህለሁ፤ ደግሞ ታሳዝነኛለህ። እንደ አባት ከጎንህ ሆኜ ባሳድግህ ደስ ይለኛል፤ ግን ላሳድግህ የምችል አይመስለኝም..." እያለ ሲያወራው እሰማለሁ ያለችው ሰርካለም፤" ህፃኑ አባቱ ያለው ምን ማለት እንደሆነ ቢገባው፤ ምን ይሰማው ይሆን?" በማለት "እንኳንም አልገባው" ብላለች።

ሰርካለም እንደምትለው፡- እስክንድር ልጁን በሰላም እንደማያሳድገው ያውቅ ነበር፤ ምክንያት፡- ለእስክንድር የሀገሩ ነገርና የህዝቦቿ ነፃነት ጉዳይ ከልጁም በላይ ዋጋ ያላቸው ናቸው።

"ናፍቆት አድጎ ትልቅ ሰው ሲሆን ያኔም ይህች አገር እንዲሁ ከሆነች፤ ታጋይ እንደሚሆን አምናለሁ" ያለችው ጋዜጠኛ ሰርካለም፤ "እስክንድር አስመሳይና የተገኘውን በልቶ የሚያድር ልጅ እንዲኖረው አልመኝለትም። እስክንድር በመረጠው መንገድ ሳቢያ ምንም የስቃዩ ሰለባ ብሆንም፤እሱን የማይተካ ልጂ እንዲኖረው አልመኝለትም"ብላለች።

የተወለደ ልጅ ነው።አሁን ደግሞ በ 5 ዓመቱ አባቱ በፖሊሶች ተከቦ በካቴና ሲታሰርና ሲንገላታ አይቷል። አባቱ-እሱ ወደተወለደበት ወህኒ ቤት መግባቱንም እያየ ነው። ማንበብ ሲችል፤ እነዚህን የሚፃፉትን ፅሁፎች ሁሉ ያነባል። ያኔ አባቱ በህይወት ባይኖርም፤ አለያም እስር ቤት ቢኖርም አለያም ከእስር ተፈትቶ አብሮት ቢኖርም፤ የማን ልጅ እንደሆነ ያውቃል። ከዚህ ልጅ ምን ይጠበቃል?"ስትልም አክላለች-ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል።

ሰርካለም አያይዛም፡-"አባቱን በካቴና አስረው ቪዲዮ ሲቀርፁትና ፎቶ ሲያነሱት፤ ህፃኑ "አባቴን"እያለ መሬት ላይ ወድቆ እየተንከባለለ ያለቅስ ነበር።ያኔ ፖሊሶቹ ገለል ሊያደርጉት ሲገባ፤አብረው ቪዲዮ ይቀርፁታል።ይህ ዘግናኝ ድርጊት ለየትኛው ሁኔታ መረጃ እንደሚሆን እነሱ ናቸው የሚያውቁት"ብላለች።

እስክንድርን ከዓላማው የምትጎትተው ሰው ባትሆንም፤አንዳንድ ጊዜ፡- "አረ እባክሽ ተው በይው!" የሚል ጉትጎታ ሲበዛባትና እግር እግሩን የሚከታተሉት ደህንነቶች አላስኬድ አላስቀምጠው ማለታቸው ሲበዛ ፡-"እስቲ ለእነሱም እረፍት ስጣቸው፤ አንተም አረፍ በል" ስትለው፤ "አንቺም እንደዚህ ትይኛለሽ? ታዲያ አንቺ እንደዚህ ካልሽን፤ሌላ ማን አለኝ?" ይላት እንደነበርም ሰርካለም አውስታለች።

"ይህን የምለው ሚስቱ ስለሆንኩና አንድ ልጃችን ስለሚያሳዝነኝ እንጂ፤ ዓላማውን ሳልደግፍና ሳልኮራበት ቀርቼ አይደለም" ያለችው ሰርካለም፤" እስሩን፣ ስጋቱንና ፍርሀቱን ለምጄዋለሁ። እስክንድር ከእንግዲህ በሁዋላ ከእስር ቤት ቢወጣ እንኳ፤ ራስ ወዳድ፣ ያየውን እንዳላየ የሚሆን፣ ፈሪና ልምጥምጥ እንዲሆን አልፈልግም፤ እኔ ብፈልግ እንኳ እንደማይሆን ስላወቅኩትም ይሆናል ይህን ያልኩት"ብላለች።

ሰርካለም ፅሁፏን ስትቋጭም፡_የእውነት፣ የፍትህና የነፃነት ጉዳይ እስክንድር ትልቅ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ናቸው።ብዙ የተንገላታባቸውና ሁለት መልክ ያወጣባቸው ቁም ነገሮች ናቸው።ጠ/ሚ/ር መለስ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አቋርጠው ጫካ ገብተው እንደታገሉት ሁሉ፤ እስክንድርም ያጣውን አጥቶ ከደረሰበት በላይ መከራ ቢደርስበትም እንኳ፤ እንዳይታገል ማድረግ አይቻልም። የአቶ መለስና የእስክንድር የትግል ስልቶች የሚለያዩት፤ እርሳቸውና አጋሮቻቸው ጠመንጃ አንስተው መዋጋታቸውና እስክንድር ደግሞ ፍፁም ሰላማዊ የሆነውን ትግል መምረጡ ነው"ብላለች።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz**

**እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። <u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org